ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ቅጽ 33 ቁጥር 2 ኅዳር 2000 ዓ.ም.

# አዲስ ዘመን ፤ቀጣይ ሕዝባዊ ትግል

ምዕተ ዓመቱ አልፎ አዲሱ ሲመጣና በተለይም የወያኔ አገዛዝ ሚሌኒየም በሚል ስያሜ ዝርፊያና ዳንኪራ ዓመቱን ሙሉ በመቀጠል ሊያካሂድ ሲነሳ ኢሕአፓ የመጪው ዘመን አካል እንደመሆኑ መጠን መገምገምና በልሳኑ ማቅረብ ቢገባውም በነበረበት ችግር አልቻለም ነበር፡፡ ከመቅረት መዘግየት ይሻላል ነውናም ዛሬ በኅዳሩ የመስከረሙን ሂሳብ ለማወራረድ መነሳታችን ባለፈው ምዕተ ዓመት ቢያንስ ለ35ቱ ዓመታት ያካሄድነውን ሕዝባዊ ትግል መቃኘቱ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ አዲስ ዘመን ገብቷል፤ ሕዝባዊ ትግላችን ግን አሁንም ቀጥሏል፡፡ የሰማዕታት ዝክርም በዚሁ እንደገና መደረግ ያለበት በመሆኑ ኤሎሄ ለሚለው ደማቸው በትግላችን ምላሽ መስጠቱን ቀጥለናል፡፡

የአፄው መንግሥት ከዘመኑ ጋር ለመሄድ አቅቶት በሕዝብ ላይ የጫነው ኋላቀር ሥርዓትም ብዙኀኑን ለገባርነት-ጢሰኝነትና ለጭቆና ዳርጎ ባለበት፥ በሰፊው ሕዝብ ላብ የተማሩት ወጣቶች አንደበት ላጣው ሕዝብ ተሟጋች በመሆን ቀደም ሲል ሲፈሩ ሲቸሩ ይለማመኑት የነበረውን ሥርዓት አውግዘው መሬት ለአራሹ ብለው ደፍረው ከተሰለፉ ጊዜ ጀምሮ አዲስ የትግል ታሪክና ምዕራፍ መፃፍ መጀመሩ ይታወቃል፡፡ ሥርዓቱ በራሱ ሊታደስ ሊሻሻል የሚችል አልነበረምና ከአንዴም ሁለት ሶስቴ መፈንቅለ መንግሥት ተሞክሮበት በአፈና ከመወጣት በስተቀር ትምህርትን አልቀሰመም፡፡ አፄው ዘመናዊ መሪ ተብለው በባዕድ ሲወደሱ በሀገር ውስጥ ግን ሥርዓታቸው አምባገነናዊ እንደነበር ገፈቱን የቀመሰውና ግፉን የተሸከመው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው ነበር፡፡ የፖለቲካ ነፃነቶች ሁሉ ተከልክለው፤

ብዙኀኑ አርሶ አደር ምርቱን እየተቀማ፣ ብዙኀኑ በብሔረሰብም ሆነ በሃይማኖት ደረጃ ልዩነት መሸከምን ተገድዶ፣ የሀገር ሉዓላዊነት የጦር ሰፈር በከፈተ ባዕድ ሀገር ተደፍሮ ሕዝብም በድህነት ለረሀብ ተጋልጦ የነበረበት አገዛዝ ዘመናዊነቱ ሆነ ፍትህ አንጋሽነቱ ከሕዝብ ተሰውሮ ቢከርም የሚያስገርም አልነበረም። ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ከኋላ ተነስተው በተሻለ ሁኔታ ሲገኙ፣ በዓለም ደረጃም የለውጥና አብዮት ነፋስ እየነፈሰ ሲመጣ ኢትዮጵያም ከዚህ ማምለጥ አትችልም ነበርናም ተማሪዎች ለሥር ነቀል ለውጥ ተንቀሳቀሱ። ወጣቶቹ በሰላም መሬት ለአራሹ ብለው ሲሰለፉ ሥርዓቱ የሰጠው ምላሽ ኃይልን መጠቀም ነበር። ይህ ሁኔታ ባለፈው የምዕተ ዓመቱ መጨረሻ ግማሽ አገዛዞችን ከሕዝብ የሚለየው ገደል ሆኖ ቀርቷል። ሕዝብ ለመብቱ ሲጮህ ምላሹ ጥይትና አፈና መሆኑ፣ ለሰላማዊ ትግል ምላሹ ጭፍጨፋና አፈና መሆኑ በዚያን ጊዜ ለነበረው ትውልድ የቅርብ ትዝታ ነው። ያለፈው ምዕተ ዓመት ያፈራቸው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓቶች ወይም አገዛዞች ሁሉም በተለያየ የክፋትና አረመኔነት ደረጃ ቢሆንም መሠረታዊ ይዘታቸው ፀረ ሕዝብና ሽብርተኛ መሆኑ ተጋልጧል።

የተማሪዎቹ ትግል አዲስ የታሪክ ምዕራፍን ጀምሮ ኢትዮጵያን ከጨለማ ወደ ብርሃን ለመውሰድ የምሥራች ዕምቢልታን አሰማ። ሀገራችንም ከዚያን ጊዜ ወዲህ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ እንደማትሄድ አበሰረ ። ቀሰ በቀስ እየተጠናከረ የመጣው ይህ እንቅስቃሴም በርዕዮቱም መስክ እየጠራና መፍትሔዎችንም በተጨባጭ ግምገማ አጅቦ ሊያቀርብ ወደሚችልበት ደረጃ ደረሰ ። የዚያን ጊዜ እንቅስቃሴ ግራ ክንፍ መሆኑን በደፈናው የሚያወግዙ ክፍሎች ሊረዱት ያልቻሉት ሐቅ ቢኖር፥ በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ለውጥ ፈላጊ እንቅስቃሴ ግራ ክንፍ ከመሆን ሌላ ምንም አማራጭ እንዳልነበረው ነው። በኢትዮጵያ የካፒታሊዝምን ሥርዓትና ውሱን ዴሞክራሲውን ሊያሰፍን የሚችልና ከገዢው ክፍልም የተቃረነ መደብ አልነበረም። ከበርቴዎቹ ከሥርዓቱ የተቆራኙና ከባዕድ ተያይዘውም ነፃ ያልሆኑ የአቀባባይ ሚና ያላቸው ብቻ ነበሩ። ከዚህ ባሻገር መለስተኛ ለውጥ ወይም የጥገና ለውጥን የሚያስተናግድ ሥርዓት ባለመሆኑ ከሥረ መሠረቱ ተነቅሎ መወገዱ የግድ አስፈላጊ ነበር። በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ በየአህጉሩ የሚካሄደው የነፃነትና የመብት ትግል እንዳይሳካ ከደቡብ አፍሪካ ዘረኞች ጋር ሳይቀር ተጣምሮ የሚንቀሳቀሰው አሜሪካ በመሆኑና የሕዝብ አንቅስቃሴዎች የሚደገፉት በሶሻሊስት ሀገሮች ስለነበር ግራ ክንፍ አስተሳሰቦች መስፋፋታቸው የሚጠበቅ ነበር። የኢትዮጵያን ችግሮች ወጣቶች ሆኑ ለጥቆም ኢሕአፓ አልፈጠሯቸውም። ሥርዓቱ የቀፈቀፋቸውን ውስብስብ ችግሮች ሊፈቱ ሞከሩ እንጂ የሌለን ችግር ቆስቁሰው ከዚህም ከዚያም አላመጡም። ሐቁን ስናይ ደግሞ ተማሪዎች ለትግሉና ለሕዝብ መስዋዕት ከፍለዋል--ከጥላሁን ግዛው እስከ ዋለልኝና ሌሎችም ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

የለውጥ እንቅስቃሴው ለጥ ያለ ጎዳና አግኝቶ አልተጓዘም። ከተማሪው እንቅስቃሴ የተፃረሩ ተማሪዎች ጥቂቶች አልነበሩም። በገዢው ክፍል ጎን የተሰለፉ፣ ለባዕድ ያደሩ፣ ፀረ ለውጥ የሆኑት ቢበዙም በቆራጥነት ትግል ብዙኀኑ የሕዝብ ወገን ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ለትግሉ ስኬት ደግሞ የታጋዩ ክፍል በአንድነት መቆሙ ወሳኝ ነበርና የኢትዮጵያ ልጆች በብሔረሰብ ደረጃ የማይከፋፈሉበትንና እኩልነት የሚኖርበትን ሁኔታ እውን ለማድረግ እንቅስቃሴው የብሔረሰብን ጭቆና ተቃውሞ መገኘቱ ግዳጁ ነበር። እንቅስቃሴው ገና መሬት ለአራሹ ብሎ ትግል ሳይጀምር በኤርትራ ትጥቅ ትግል ተጀምሮ ነበር። እንቅስቃሴው ገና ነቃሁ፥ አለሁ ሊል ሲነሳ የሜጫ ቱለማ ትግል ተጀምሮ ነበር። በኦጋዴን፣ በባሌ ወዘተ የነበሩት እንቅስቃሴዎች ከተማሪው ትግል በፊት የተወለዱ ነበሩ። ይህን ፈጦና አይሎ የመጣ ችግር፥ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴም ሆነ ኢሕአፓ አላየንም ብለው የሚያልፉበት ሁኔታ አልነበረም። ምላሽ ጠያቂ ችግር ነበርና የበኩላቸውን ማለትም ጭቁኖችን ያሰባስባል፥ ያስተባብራል፥ እኩልነትንም ያመጣል  ያሉትን ምላሽ በጊዜው ሰጥተዋል። ይህም ባለፈው ምዕተ ዓመት ቦታ ተሰጥቶት ሊመዘን የሚገባው ጉዳይ መሆኑ አያከራክርም። በወቅቱ የነበሩ በርካታ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታዛቢዎች በመዋዕለ-ዜናቸው ያሰፈሩት የታሪክ ሐቅ ነው።  የዚህም ትግልና ብስለት ውጤት የሆነው ኢሕአፓ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ለማታገል መቻሉና ሕብረ-ብሔራዊ ሆኖ የጠባቦችንም ዘመቻ ሊያጋልጥና ሊዋጋ በቦታው መገኘቱ በዚሁ አንፃር የሚታይ ነው። የሕዝባዊ ዴሞክራሲ ሥርዓት አማራጭም ሲወሰድ ለጥቂቶች ብቻ የሚሆን ውሱን ዴሞክራሲ ለሕዝባችን የማይበጅ መሆኑ ታምኖበትና ለብዙኀኑ ያልሆነች ኢትዮጵያ ለጥቂቶች መፈንጨያ መሆን የለባትም ከሚልም መሠረታዊ እምነት በመነሳት ነው። የታሪክን ሐቅ በጊዜ አልፏልና ተዘንግቷል ላፒስ ሊያጠፉ የሚከጅሉ እንደሚሉት ሳይሆን፥ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴም ሆነ ኢሕአፓ በፅኑና ንፁህ ሀገር ወዳድነትና ሕዝብ አፍቃሪነት ተነሳስተው ለሕዝብና ለሀገር መሰዋዕትነት የከፈሉ ናቸው። በዚህም ባለፈው ምዕተ ዓመት ላይ ታሪክ የሚያከብረው ማህተማቸውን አትመውበታል።

የተማሪው እንቅስቃሴ በነበረው ሁኔታ ገዝፎ፥ ከሚናው በላይ ኃላፊነትን ተሸክሞ የነበረውን ኢሕአፓ በ1964 ዓ.ም. ተመሥርቶ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ድርጅት ሚናውን ሲቀበል፥ ይህ ጊዜ ደግሞ ሌላ ታሪካዊ ወቅት ነበር። የተሰበጣጠረው ትግል ሲቀናጅ፣ የፖለቲካ ድርጅት እጦት ሲወገድ፣ ላቅ ወዳለ የትግል ደረጃና ስልት ሽግግር ሲጀመር፥ ታሪክ ተሰርቷል። ድርጅት የተፈጠረበት ቀን ወያኔ  እንደሚለው የጭቁኖች ልዩ ፀሐይ በራላቸው ማለት ማጋነን ቢሆንም፥ የኢሕአፓ ምሥረታ የትግሉን ይዘትና አካሄድ ቀየረው ቢባል ስህተት አይሆንም። በታሪክ አጋጣሚ በዚህ ድርጅት ምሥረታ ከተካፈሉት ውስጥ አብዛኞቹ

በህይወት ዛሬ ባይኖሩም፥ የመስራቾቹ ብሩህ ተስፋና ሕዝባዊ ቃል ኪዳን እነሆ ስንቱን ዓመት፣ ስንቱን መከራና ፈተና አልፎ፥ ዛሬም ኢሕአፓን ገላጭ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህ በደምና በመስዋዕት ታጅቦ የመጣው ክስተት ስጋጃ ተነጥፎለትና ሁሉም ነገር ቀንቶት የመጣ ሳይሆን፥ ውሱን ተመክሮና ዕውቀትን ከራዕይና እምነት፥ ከሀገር ፍቅርና ሕዝብ ወዳድነት ጋር አቆራኝቶ፥ ችግርና መከራን በተግባር ሊጋተር ቆርጦ የተነሳ ነበር፡፡ በመሆኑም በህቡዕ ለመደራጀትና ለማደራጀት፣ የሕዝባዊ ሠራዊት እርሾ የሚሆነውን ኃይል ለማዘጋጀት፣ ሕዝብን ለማንቃትና ግዙፍ መስሎ የተሰየመውን አገዛዝ ለመታገል ሲጀምር፥ ከዚያን ወቅት ጀምሮ ወደ ኋላ መመለስ የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጠረ ፡፡ ሥርዓቱ እንደ ቀድሞው ሊገዛ የማይችልበት ሁኔታም መከሰት ጀመረ ፡፡ ሕዝብም ለለውጥ መነሳሳቱ ታየ፡፡ ጎድሎ የነበረው ድርጅት አቅም ባይኖረውም፥ ቦታውን ሊይዝና ሚናውን፥ግዳጁን ሊወጣ ተዘጋጀ ፡፡ የየካቲት 66 አብዮት ፍንዳታም በዚህ ጊዜ ነበር፡፡ ለዚህም መንገድ የጠረጉትንና ስማቸው ባይጠራምና ባይታወቅም ብዙ መከራ የተቀበሉት ጅግኖችን ዛሬም የምንዘክራቸው ነን፡፡ ለሰራዊት ምሥረታው ውድ ህይወታቸውን የሰጡትን፥ ብንያም አዳነንና መሀመድ ማህፉዝንም በተለይ ሳናነሳቸው ማለፍ አንችልም፡፡

የየካቲት 66 አብዮት የፈነዳው በግብታዊነት ነው ቢባልም፥ ለሁኔታው መከሰት ቀደም ሲሉ የተካሄዱት ትግሎች ሁሉ የማይናቅ አስተዋፅዖ አድርገዋል፡፡ እነ መንግሥቱና ገርማሜ ንዋይ፥ እነ ደጃች ታከለ ወልደ ሃዋርያት፥ እነ አበራ ገሙ፥ እነ ጥላሁን ግዛው፥ የደራሳና ጎጃም አርሶ አደሮች፥ የተጋዙት ተቃዋሚዎች፥ ተማሪዎችና ምሁሮች፥ የተሰደዱትና በሱዳንና የመን ታፍነው የተገደሉት፥ እምቢኝ ብለው ለስቃይ የተዳረጉት ሁሉ፥ የታወቁት ብቻ ሳይሆን ስማቸው ያልተጠራው ጀግኖች ሁሉ ለየካቲት አብዮት ድልዳል ሆነዋል፡፡ ይህ የሕዝብን ብሶትና ምሬት አቅፎ የፈነዳው አብዮት፥ ኢትዮጵያውያንን በኢትዮጵያዊነት ያሳተፈ፣ እስላምና ክርስቲያኑን ያስተቃቀፈ፣ ወጣቱንና አዛውንቱን ያገናኘ፣ ሲቪሉንና ወታደሩን ያስተባበረ የሥርዓቱን ቅስም ሰባሪና ቀብር አብሳሪ ነበር፡፡ አብዮት የጭቁኖች ፈንጠዚያ ነው የተባለው በየካቲት አብዮት ተረጋግጧል፡፡ የአድሃሪ ገዢዎች ትጥቅና ኃይል ሕዝብ ቆርጦ በተነሳበት ወቅት የወረቀት ነብር ከመሆን እንደማያልፍም ታይቷል፡፡ የተራበውን ሕዝብ የረሱት ገዢዎች ቁንጮ የነበሩትም አፄ ሎሌዎቼ ይሏቸው በነበር መኮንኖች ወደ ወህኒ ሲወሰዱ፥ የሥርዓቱን መንኮታኮት ከማብሰሩ ሌላ ተኪ ሊሆኑ ያቆበቆቡት መኮንኖችም ልበ ሻካራ መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡ ፍትህን ለሕዝብ የነፈገው ገዢ መደብ ራሱም ፍትህን ተነስቶ በወታደራዊ ውሳኔ ለሞት ተዳረገ ፡፡ መኮንኖቹ ተክተነዋል ካሉት ሥርዓት ልዩነታቸውም በዚያው መደብዘዝ ጀመረ ፡፡ ያለፈውን ምዕተ ዓመት ስናነሳ፥ የየካቲት 66 አብዮት፥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ሲሆን፥ አብዮት ስንል ደግሞ ኢሕአፓ በዚሁና በቀጣዩ ትግል የነበረው ቦታ ደግሞ ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም፡፡

የአንድ አብዮት ወይም ሕዝባዊ ትግል ድል የሚለካው ያለፈውን ሥርዓት በመጣሉ ብቻ ሳይሆን የተሻለና ሕዝባዊ ሥርዓት በመመስረቱ ነው እስከተባለ ድረስ የየካቲት አብዮት ድልን አልተጎናፀፈም፡፡ የሕዝብን ድልና ሥልጣን ምርጥ መኮንኖች ቀሙት፡፡ ሕዝብ የሚበጀውን አያውቅም፤ እንደ ህፃን ነው ይሉ የነበሩት አፄ ሲወገዱ፤ ሕዝብ ሞግዚት ያሻዋል አለበዚያ ተንኮለኞች ያወናብዱታል የሚል የመኮንኖች ጥርቅም በሥልጣን ተሰየመ፡፡ ታጥቦ ጭቃው ሲጀምርም ኢሕአፓ ይህንኑ በማጋለጥና ሕዝብን ቀስቃሽ በነበረችውና አሁንም በሆነችው ልሳኑ በዴሞክራሲያ አማካይነት ሥልጣን የሕዝብ ናትና ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመጓዝ ሁሉን አቀፍ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም በሚል ትግሉን አጧጧፈ ፡፡ ይህም ትግል ሰላማዊ በሆነ መንገድ በፖለቲካው መስክ፤ በተቃውሞ ሰልፎችና የሥራ ማቆም አድማዎች አማካይነት የተካሄደ ቢሆንም÷ ያገኘው ምላሽ ቀደም ስንል እንዳቀረብነው ያው አፈናና እመቃ ከመሆን አላለፈም፡፡ እስራቱና ግርፋቱ ቦታውን ለግድያ ለቀ እነ አሊ ሙሳና ጌታቸው ሺበሺ በሕዝብ ላይ እንዳበደ ውሻ ተለቀው ፍጅት ሲያካሂዱ ለማየት በቃን፡፡ የተሳሳተ ግምገማ ያደረጉ የተወሰኑ ምሁራንም ለምርጥ መኮንኖቹ ሂሳዊ ያሉትን ድጋፍ በመስጠታቸው የተደናበረውን ቡድን÷ በተወሰነ ደረጃ ሊያጠናክሩትና ለተከተለውም ሽብርና አረመኔያዊ ግድያም ማጠየቂያ ሊያቀብሉት መቻላቸውም በታሪክ የተመዘገበ ነው፡፡ በፖለቲካው መስክ ሽንፈትን የተከናነበው ደርግ ተብዬው ጥርቅም ችግሩን ለመወጣት÷ በኢሕአፓ ላይ ጦር አውጆ በይፋ ፍጅቱን ተያያዘው፡፡ ሐቁ ይኸ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ታሪክ በራዦች ዛሬ ኢሕአፓ የሰላም ትግልን እምቢ ብሎ ተኩስ ከፈተ ብለው ሀሰት ማውራቱን መርጠዋል፡፡ የሕዝብ አብዮት ድሉ ለሕዝብ እንዲሆን፤ ዴሞክራሰያዊ ሥርዓት እንዲመሰረት÷ ሥልጣን ከሕዝብ እጅ መነጠቅ የለበትምና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ሲል ኢሕአፓ ያደረገው ጥሪ ጆሮ አግኝቶ ተደምጦ ቢሆን ኖሮ÷ ዛሬ የምንገኝበት የስቃይ ሁኔታ በተወገደ ነበር፡፡ የታሪክ ዓይናችንን ወደፊት ብንወስደው ደግሞ በ1983ም የጥቂቶች የሽግግር መንግሥት ምስረታ ደባ ለወያኔ ይጠቅማል እንጂ ለሀገር መዘዝ ነው ሲል ኢሕአፓ ያቀረበው ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ብሎ ማሰብም ይቻላል፡፡

አንድ ገዢ መደብ የሕዝብን ተቃውሞ ለማፈን÷ ወይም የፍርሀት ድጋፍ ለማግኘት ወደ ኃይል መጠቀምና ግድያ ሲያመራ÷ ሽንፈቱን ያረጋግጣል፡፡ ወደ ውደቀቱ ይጠርም ይርዘምም ጉዞ መጀመሩንም ይጠቁማል፡፡ በኢትዮጵያ ምድር የተካሄደው ቀይ ሽብር የደርግ አገዛዝን ሽንፈትን ያረጋገጠ እንጂ÷ በሽብሩ የተጠቃውን ኢሕአፓን ከታሪክ ገፅ መጥፋት ያስከተለ አልነበረም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው ነው የሆነው፡፡ የኢሕአፓ አባላት መስዋዕት ሲቀበሉ የጀግና ታሪክ ጽፈዋል፡፡ ዛሬ የሰፈነውን ተንበርካኪነት ስናይ ደግሞ

*እነዝያ ብርቅዬ የእናት ኢትዮጵያ ልጆች፤ ድል ለሕዝብ ብለው በደማቸው ጽፈው የተሰዉት፤ እናቸንፋለንና ውድቀት ለፋሺስቶች ብለው እየጮኹ በውድቅት የተረሸኑት፤ ስቃይ የተቀበሉት፤ ወህኒና መሰል የስቀይ ማጎሪያ ቦታዎች ፍዳ የተቀበሉት፤ ለመጪው ትውልድ አርዓያ የሚሆን ታሪክን በቆራጥነት ጽፈው የማለፍን ዕድል አግኝተዋል። ቀይ ሽብሩ በአንድ በኩል የፋሺስቶቹን አረመኔነት በአሰቃቂ መልክ ሲያጋልጥ በሌላ በኩል ደግሞ የኢሕአፓን ቆራጥነትና ፅናት፤ ሞት አይፈሬነትና ሀገር ፍቅር አስመዝግቧል። ህይወትን ለሀገር ከመስጠት በላይ የሀገር ፍቅር አለን? ትግል ቀለም መንዳት ወይም ቃላትን ማንበልበል ብቻ ሆኖ የሚታያቸው ክፍሎች ዛሬም በዚያ መራራ ትግል ወጣቱ አለቀ፤ ድርጅቱ አስጨረሰው ወዘተ እያሉ የለመደች ጣታቸውን ወደ ጥቆማ ቢቀስሯትም፤ ታሪክ የመዘገበው ሐቅ ግን የሕዝብ ስርየትና የሀገር ሉዓላዊነት ያለቆራጥ ትግልና መስዋዕት ሊገኝ እንደማይችልና ያ ጀግና ትውልድ ደግሞ በቃሉና ቃል ኪዳኑ ፀንቶ ሁናቴው ሲጠጥር ሽብረክ እጥፍ ሳይል ለዓላማው መሰዋቱን ነው። ይህ ሊወደስ ሊከበር የሚገባ የጀግንነት ታሪክ በየእስር ቤቱ፤ በየስቃይ መቀበያው የከረፋ ቦታ ሁሉ፤ ርሸና በተካሄዱባቸው ጫካዎችና የመቃብር ቦታዎች ሁሉ ተጽፏል። ስማቸው ብዙ ነው፤ ስማቸው ህያው ነው፤ ታሪካቸው ማፈሪያ አይደለም-የሚያኮራ እንጂ። ባለፈው ምዕተ ዓመት የኢሕአፓ ጀግኖች የቆራጥነትና የጽናት ትርጉም ምን እንደሆነ አስፍረው አልፈዋል።*

*በፋሺሰቶች በአንድ በኩል፥ በጠባብ ብሔርተኞች በሌላ በኩልና ከዚያም በፀረ ኢትዮጵያ ባዕዳን ጥቃት የደረሰበት ኢሕአፓ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ሳያሳልፍ ታግሎ ያለፈውን ምዕተ ዓመት ሸኝቷል። ይህም ሌላ ሳንጠቅሰው የማናልፈው ጉዳይ ነው። መከራ ስቃዩ በዛ ብሎ ለአረመኔዎቹ እጅ አልሰጠም። ሹመት ሲሉት አቤት ብሎ አላጎበደደም። ሀገርክን ሽጥና ተጠቀም ሲሉት "እዘዙኝ ተከዜን ድልድይ ላፍርስላችሁ" ብሎ አልተሰለፈም። ኃያል መንግሥት ብሎ ለባዕድ አልራደም። ቢሆንም ይህ ሁሉ ደግሞ ከኢዮብ ያላነሰን ፈተና መቀበልን የግድ ብሎበት ያለፈ እንጂ ቀላል ሂደት አልነበረም። ትግሉ ከረር ሲል ለባለነፍጡ ጎንበስ እንበል ያሉ ጥቂቶች ለዚሁ ማተብ በጣሽነታቸው ማጠየቂያዎችን በውብ ቃላት ሸፋን ደርድረው በአንጃነት አፈንግጠው በድርጅቱ ላይ ይህ ነው የማይባልን ጉዳት አደረሱበት። በሌላ በኩል ደግሞ የብሔረሰብ መብት ጥያቄ በግንጠላ ብቻ ነው የሚፈታ ይሉ የነበሩት የዛሬ ባለሥልጣኖች መሰል አጋሮችን ይዘው በኢሕአፓ ላይ ጦርነት በትግራይ ከፈቱ። ይህ ዘመቻቸው ያው ሥልጣን እስኪይዙና ከዚያም በኋላ የቀጠለ ነው። የአንጃው ተውሳክ ወደ ኢሕአፓ ሠራዊትም ጊዜውን ጠብቆ ብቅ ቢልም፥ብዙ ጉዳት ሳያደርስ ሊገታ ችሏል። በአንፃሩ ግን በትግሉ ላይ ተስፋ የቆረጡ ጥቂቶች ብዙዉን ታጋዩን አባል ተስፋ በማስቆረጥና በጎረቤት ሀገር ተስብስበን እንመለሳለን ብለው በማደናገር ያካሄዱት የብተና እንቅስቃሴ ሰራዊቱን በከፍተኛ ደረጃ ጎድቶት ዳግም ግንባታ ጊዜና*

ህይወትም ጠይቋል። እነ ጂጋር፤ ስበር፤ በርሔ፤ ጉግሳ፤ ብርሃኑ፤ ፅጌ ፤ ሀዲሽና ሌሎችም የተሰዉት ሁሉ የሚጠቀሱ ናቸው። የዚሁ እንቅስቃሴ አባወራዎች ዛሬም ቢሆን በፀረ ድርጅትነታቸው የቀጠሉ መሆናቸው ሲታወቅ ከእነ ስመ ጥሩ ብአዴን ተብዬዎች ቁንጮዎችም መረዳት የሚቻል ነው። ዛሬ ድርጅቱ 35 ዓመት ህልውናውን ጠብቆ የቆየው ይህን መሰል ውጣ ውረዶችን እየተቋቋመ፤ የውስጥና የውጭ እሾኮችን እያራገፈ ነው። ምዕተ ዓመቱ አበቃ አለፈ ስንልና ለአዲሱ ዘመን ራሳችንን ስናዘጋጅ ከዚህ ሁሉ እየተማርን ዛሬም ኢሕአፓ ለማንም ፀረ ሕዝብ ሳይጎነበስ ሕዝባዊ ቃል ኪዳኑን እንዳከበረ ትግሉን ይቀጥላል በሚል መንፈስና ቆራጥነት ነው።

ወደ አዲሱ ምዕተ ዓመት ስንሸጋገር ያለፈውን ውዝፍ የኅብረተሰብ ዕዳን ከሞላ ጎደል ተሸክመን ነው። በወጪው ብዙ ሰርተናል። የፖለቲካ ድርጅትን ምንነትንና አስፈላጊነት፤ የሕዝብ መብት መከበር እንዳለበት፤ በብሔረሰብ፥ በፆታ፥ በሃይማኖት እኩልነት መስፈን እንደሚኖርበት፤ አንድነት በዴሞክራሲ ላይ መገንባት እንደሚገባው፤ ስለ ሕዝብ ኃያልነት፤ ስለ ሀገር ሉዓላዊነት ወዘተ ይህ ነው የማይባል ዕውቀትና ግንዛቤን በትግልና በገበርነው ደም አሰጨብጠናል። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም አምባገነን የሚያታልለው ሳይሆን፥ መብቱና ጥቅሙን የሚያውቅ ሕዝብ ነው። ለዓመታት የተቃጣበትንም የክፍፍል ዘመቻ ተቋቁሞ ሀገሩን እስካሁን ሊጠብቅም ችሏል። ተለጣፊው ቢበራከትም ለሕዝብ የሚታገሉ ድርጅቶችም ተቋቁመዋል፤ ኅብረታቸው ገና ያልተገባደደ መንገድ ቢቀረውም ብዙ ተጉዟል። ሆኖም ባለፈው ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች የሆኑት ዛሬም ምላሽ አላገኙም። መሬት የአራሹ አይደለችም። ድህው ከድህነቱ አልተላቀቀም-- ተገቢ ትምህርትና የጤና እንክብካቤ ተነፍጓል። የብሔረሰብ እኩልነት የለም። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አልተገነባም። የሕግ የበላይነት ደብዛውም ጠፍቷል። የሕዝብ መሠረታዊ መብቶች ተረግጠዋል። ዛሬም የእስረኛውን ቁጥር ጉድጓዱና ማጎሪያው ይወቀው እየተባለ ነው። ጓዶቻችንና ዜጎች ተይዘው ደብዛቸው ጠፍቷል። ኢትዮጵያ ለባዕድ ተሸጣ ልጆቿ በማይመለከታቸው ጦርነት ገብተው ለዕልቂት ተዳርገዋል። አገዛዙ ፍጅት ያካሂዳል፤ ረሀብም ሰፍኗል፤ ሥራ አጡ በሚሊዮኖች ነው--ግን መንደላቀቁ የጥቂቶች ናት። በአፄውና በደርግ ስር ያለፈው 61 ዓመት በወያኔ አገዛዝ 17 ዓመት ሲደመር የዛሬው ካለፈው ከፍቶ፤ የሀገር ህልውና ራሱ ለከፋ አደጋ ተጋልጦ ያለበትን ሁኔታ ማየት እንገደዳለን። የተሰዉ ጓዶቻችን፤ ለሀገራቸው ህይወታቸውን የሰጡ ዜጎችም ዳግም ተነሱ ብለው ለቆራጥ ትግል ሊጠሩን ተገደዋል። ግዳጁ ገና ነውና። ኢትዮጵያ ከተወሳኮቿ አሁንም አልፀዳችምና። ችግሮቹ ስላልተወገዱ ማስወገጃው ትግል ሊታለፍ ወይም ሊተው አይቻልምና። ጠላት ያው በቦታው በጠላትነት ሰፍሮ ያጓራልና ለዛሩ ማርከሻ የሆነው ትግል

ሊፋፋም ይገባዋል እንጂ ጨርቅን፥ ህሊናንና ወኔን ጥሎ ከጠላት ጋር ጉሮ ወሸባዬ የሚታሰብም ሊሆን አይገባውም።

ባለፈው ምዕተ ዓመት የተካሄዱት ትግሎች ሁሉ የመጨረሻ ግባቸውን ባይመቱም፤ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና ሕዝባዊ ሥረዓት ገና ባይመሰረትም፥ እያንዳንዱ ትግል በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተፅዕኖውን እያሳረፈና ይነስ ይብዛም የለውጥን ሚዛን እየጨመረ መሄዱ ደግሞ ሊዘነጋ የሚገባው አይደለም። የፖለቲካ ሥልጣን ጉዳይ ወሳኝ ቢሆንም ሥልጣን የያዘ አሸናፊ ያልያዘ ደግሞ ተሸናፊ ነው ብሎ በጅምላ መደምደም ደግሞ ከፖለቲካ አንፃር ስህተት ነው። ይህ የተዛባ አመለካከት ሲሰፍን ነው ቡድኖች ለሥልጣን በመቋመጥ ከገዢው ኃይል ጋር በመስማማት የፀረ ሕዝቡ ሂደት ተጓዳኝ፥ ተቀራማች ለመሆን ሲሯሯጡ ለማየት የተገደድነው። የሕዝብ ትግል የመጨረሻ ግቡን እስኪመታ በሂደቱ ብዙ ድሎችን እያገኘ ይሄዳል። የዚህን ሐቅነት ደግሞ ያለፈው ምዕተ ዓመት ትግሎች ውጤት ያሳያል።--ዛሬ ኢትዮጵያ በትላንቱና ትላንት ወዲያው ቦታዋ ላይ አትገኝም። ለዚህም ሁናቴዎችን ማነፃፀሩ አስፈላጊ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። ባለፈው ምዕተ ዓመት አጋማሽ በኋላ የተቋቋመው ኢሕአፓ የቀጠለው ሕዝባዊ ትግል አካል ሆኖ ቆይቷልና ዛሬ ወደ አዲሱ ዘመን ስንገባ ያለፈውን ውዝፍ ለማንሳትና ለማስወገድ፤ ምላሽ ላላገኙ መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎችና ፍላጎቶች መፍትኄ ለማግኘት ከሕዝብ ጎን ሆኖ ትግሉን መቀጠል የግድ ሆኖበታል። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ያጠወለገን በሽታ ጠፋ ለማለት ገና ባለመታደላችን፤ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ላመረረ ትግል እንደገና ጥሪ ማድረጉ የግድ ሆኗል።

ሕዝብ የራሱ የሆነ መንግሥት መርጦ ለመሰየም ያደረገው ጥረት በአረመኔ ጭፍጨፋ ስለተጨናገፈ ዴሞክራሲና መቻቻል ሰፍኖ፤ ሕዝብ በሀገሩ የሀገሩ ባለቤትና ባለመብት ሆኖ፤ የሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት ተከብሮ፤ ስደትና ረሀቡ ጠፍቶ፤ እንደቅጠል ከሚያረግፈው በሽታ ተላቅቆ፤ ቢያንስ ይህ አዲሱና መጪው ትውልድ ካለፉት በተሻለና በተለየ እንዲኖር ለማድረግ ትግሉ ገና የህይወት ግብርን ይጠይቃል። ሚሌኒየም በሚል የተደመጠው ሁካታ ጥቂቶች በዕብሪት በብዙሃኑ ላይ ሲያካሂዱት የቆየው ምፀት እንጂ ሌላ አይደለም። በዓመት ቆጠራው ደረጃ በእርግጥ አዲስ ምዕተ ዓመት በቆጠራው በሚያምኑት ተገብቷል። ወደ አዲስ ምዕራፍና ልዩ ታሪክ ግን ገና ሀገራችን አልገባችም። የየካቲት ዳግማዊ ትንሳዔ ገና ነው። እንደሚመጣ የማንጠራጠረው ለዚሁ ቀን ሳንታክት እንሰራለን፥ እንዋደቃለን። ቃል ኪዳናችንን አድሰን ከመታገል ሌላ አማራጭ የለምና ኢሕአፓ ሕዝባዊው ትግል ይቀጥላል የሚለውን መልዕክት ያስተላልፋል።

**እናቸንፋለን!!!**